Coronavirus COVID-19

safe work australia

# ለሥራ ጤንነትና ደህንነት – ስለማጽዳት

ኮቪድ/COVID-19 የሚሰራጨው በመተንፈሻ የሚፈጠር ጠብታዎች በኩል አንድ የተበከለ ሰው በሚስልበት ወይም በሚያነጥስበት ጊዜ ነው። አንድ ሰው ቫይረሱ ሊይዘው የሚችል ቫይረሱ ያለበትን ገጽታ ወይም እቃ መንካትና ከዚያም የእነሱን አፍ፣ አፍንጫ ወይም ዓይኖች በመንካት ይሆናል።

የሥራ ቦታዎች ቢያንስ በቀን አንዴ መጽዳት አለባቸው። ከዱቄት ወይም ፈሳሽ በሆነ ማጽጃና ውሃ ጋር አድርጎ ማጽዳቱ በቂ ነው።

ማድረግ ያለብዎት:

- ገጾችን ከመንካት መቆጠብ መቀነስ፣ ምልክቶችን በማስቀመጥ ደንበኞችን እንዲያውቁ ለርስዎ ሰራተኞች መርዳት
- ሰራተኞች ለሚነኩት ነጥቦች ቁጥር መቀነስ
- ከተቻለ፣ በመግቢያና መውጫ በሮች ላይ የእጅ መታጠቢያ መገልገያ ወይም የእጅ ማጽጃ ሳኒታይዘር ማቅረብ።

## እንዴት እንደሚጸዳና ነፍሳትን ማስወገድ

ከገጽታው ነፍሳት መወገዱ በፊት መጀመሪያ ማጽዳቱ ጠቃሚ ነው። ቆሻሻና እድፍ ካለ ጀርሞችን ለመግደል የነብሳትን ማስወገድ አቅም ሊቀንሰው ይችላል።

ለርስዎ ሰራተኞች ተስማሚ የሆነ ማጽጃ እና የነብሳት ማጥፊያ ውጤቶችንና የግላዊ መከላከያ መሳሪያዎች ማቅረብ እንዳለብዎት እንዲሁም እነዚህን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ስልጠና ስለማግኘታቸው ማረጋገጥ አለብዎት።

## በጽዳትና በነፍሳት ማስወግጃ መካከል ያለው ልዩነት ምንድ ነው?

**ማጽዳት** ማለት በአካል ጀርሞችን (ባክተሪያና ቫይረሶች) ለማስወገድ፡ ከገጽታው ላይ ያለን ቆሻሻና እድፍ ለማጥፋት ከዱቄት ወይም ፈሳሽ በሆነ ማጽጃና ውሃ ቀላቅሎ መጠቀም።

**የነፍሳት ማስወገጃ** ማለት በገጽታው ላይ ጀርሞችን ለመግደል ኬሚካሎትን መጠቀም ነው። ብዙጊዜ የነፍሳት ማጥፊያ ሊያስፈልግ የሚችለው ገጽታው በቫይረስ ተበክሎ ከነበረ ብቻ ነው።

## የትኛው አካባቢ ነው መጽዳትና ከነብሳት መወገድ ያለበት እንዲሁም በየስንት ጊዜ?

ብዙ ጊዜ ንክኪ ያለባት ማንኛውም ገጾች በተደጋጋሚ መጽዳት አለበት፣ ይህም እንደ የበር እጀታዎች፣ እንግዳ ማስተናገጃዎች፣ ስልኮች፣ EFTPOS እና የጋራ መገልገያዎች እንደ ሽንት ቤት ያሉት።

በግልጽ ቆሻሻ ሆነው ለሚታዩ ወይም ላደፉ ገጾች በተቻለ ፍጥነት መጽዳት አለባቸው።

በነፍስ ማስወገጃ መጠቀሙ አስፈላጊ ነው፣ ይህም በሥራ ቦታው ላይ ለኮቪድ/COVID-19 ጉዳይ ጥርጣሬ ወይም ስለመኖሩ የታወቀ ከሆነ ነው። በርስዎ ሥራ ቦታ ላይ ብዙ ሰዎች በየቀኑ የሚገቡ ከሆነ፣ በተደጋጋሚ የነፍስ ማስወገጃን መጠቀሙ ይመረጣል።

## በእኔ ሥራ ቦታ ላይ የኮቪድ/COVID-19 ጉዳይ ካለ ምን ይደረጋል?

በሥራ ቦታዎ ላይ የ COVID-19 ቫይረስ ጉዳይ ካለበት የርስዎ [አስተዳደር ግዛት ወይም ተሪቶርይ ጤና ጥበቃ ባለሥልጣን/ state or territory health authority](#) ምን ማድረግ እንዳለብዎት ይነግርዎታል። የእነሱን መመሪያዎች መከተል።

ሰዎች ወደ ሥራ ቦታ መመለስ ከመቻላቸው በፊት የሥራ ቦታዎ በሚገባ መጽዳትና ከነብሳት መወገድ አለበት።

## ስለ ሰራተኞች እቃዎችስ ምን ይደረጋል?

ሰራተኞች በሥራ ቦታ ላይ ለሚጠቀሙበት ግላዊ እቃዎች፤ እንደ የዓይን መንጽሮችና ስልኮች የነብሳት ማስወገጃ መጥረጊያን በመጠቀም በተደጋጋሚ እንዲያጸዱ መንገር አለብዎት።

## ሁሉም ነገር ከተሸጠ፤ የራሴን ነብሳት ማስወገጃ መሥራት እችላለሁን?

በመጋዘን የተገዛው የነብሳት ማስወገጃ ለመንግሥት ላወጣው ደረጃ ስለሚያሚላ ታዲያ እንደሚሰራ ያውቃሉ። ይሁን እንጂ ከመርዝ የሚያነጻ እና ውሃ ተጠቅሞ በመቀላቀል የነብሳት ማስወገጃን ማዘጋጀት ይችላሉ። ኬሚካሎች አደገኛ ስለሆኑ በሚይዙበት ጊዜ ጥንቃቄ ስለማድርግዎ ማረጋገጥ።

## የእኔ ሰራተኞች ለማጽዳት ምን መልበስ አለባቸው?

በአብዛኛው ሁኔታዎች ላይ ሰራተኞች የርስዎን ሥራ ቦታ ለማጽዳት የመከላከያ ልብስ ማጥለቅ አስፈላጊ እንዳልሆነ ነው። ሲጀምሩ:

- በአነስተኛ ጓንቶች ያስፈልጋሉ
- በኮቪድ/COVID-19 ጉዳይ የተበከለ ወይም ጥርጣሬ ለታወቀ አካባቢ ለማጽዳት የቀዶ ጥገና ጭምብሎችን መጠቀም አለበት
- ገዋኖችና ተጠቅሞ ለሚጣል ልብሶች አያስፈልግም
- የሆነ ግላዊ መከላከያ መሳሪያ ማቅረብ እንዳለብዎና የርስዎን ሰራተኞች ድህንነቱ በተጠበቀ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ ማሰልጠን ይኖርብዎታል።

## የጸረባክቴሪያ ውጤት ለኮቪድ/ COVID-19 ይገድላልን?

ጸረባክቴሪያ ውጤቶች ታቅዶ የተሰራው ባክተሪያን ለመግደል ነው። ይሁን እንጂ የኮቪድ/COVID-19 ምክንያት የሚከሰተው በቫይረስ እንጂ በባክተሪያ ስላልሆነ፤ ስለዚህ የጸረባክተሪያ ውጤት መጠቀም ጠቃሚ አይደለም።

እጆችን ለማጽዳት፤ በተደጋጋሚ ሳሙና እና ሞቅ ያለ ውሃ መጠቀሙ ውጤታማ ነው።

## ለበለጠ መረጃ

ስለ ኮቪድ/COVID-19 እና ለሥራ ጤንነትና ደህንነት የበለጠ መረጃ ለማግኘት በድረገጽ፡ Safe Work Australia website ላይ ገብቶ ማየት።